# <u>ለምን ይዋሻል? እስከመቼስ ይዋሻል?</u>

**ቁጥር** 6

ጥንት በተማሪው እንቅስቃሴ መጀመሪያ ሰሞን ማነው ኢትዮጵያዊ ብሎ ገጥሞ የነበረው ሰው ዛሬ ጊዜ አለፈና የለየለት ጠባብ ሆኖ ከታሪክ ትቢያ ወድቋል። ጥያቄው ግን ዛሬም ወቅታዊና አንገብጋቢ ነው። ኢትዮጵያዊ ማነው? ጀግና ማነው? ሀገር ወዳድ ማነው? ለመሆኑ ሀገር ስንልስ ምን ማለታችን ነው? በዚህ ሁሉ መስክስ ዋሾውን ከሀቀኛው እንዴት እንለያለን? ከባድ ጥያቄዎ ች ናቸው--ምላሽን የሚጠይቁ።

ሀገር ምንድን ናት ብለው በዱሮ ዘመን አዋቂዎች እየጠየቁ ሊያስተምሩም ሞክረው ነበር። ስለ ሀገር ሁሉም ዜጋ በቂ ግንዛቤ ነበረው ማለትም አይቻል። አንዳንድ አላዋቂዎች ብሄር የሚለውን ቃል ወጣት ተራማጆች ወይም ኢሕአፓ ፈጠረው ብለው በክስ መልክ ሊያቀርቡ ሲሞክሩ ብንታ ዘብም ሀገርን በትውልድ ቦታው ገላጭ ብዙ ዜጋ ነበር--ማለትም ሀገርህ ሲሉት ጎንደር፣ ጎጃም፣ ሸዋ፣ ከፋ፣ሐረርጌ ወዘተ ባዩ ብዙ ነበር። አሳታሚው ተስፋ ገብረ ሥላሴ ራሳቸውን ዘብሔረ ቡልጋ ይሉ እንደነበርም እናስታውሳለን። የሕዝብ እርስ በርስ ግንኙነት የዳበረ ሰላልነበረ አንዱ ጫፍ ስለሌላው የነበረው ዕወቀት የጫጫ ነበርና ሁሉን አቀፍ ብሔራዊ ስሜት ሊያድግ የቻለው ቀስ በቀስ ነው። ይህ ቢባልም ግን ጣሊያን ሀገራችንን ሲወር ሕዝቡ በአብዛኛው ሀገሬ ብሎ ተሰል ፎ ታግሏል--ከየአካባቢውም ብዙ ጀግና አርበኞች ታግለው ተሰውተዋል። ሀገር ስንል ኢትዮጵያ ስንል ለኢሕአፓ ይህ ግልፅና የማይለዋወጥ ትርጉም አለው። በመጀመሪያ ኢትዮጵያ ስንል የኢት ዮጵያን ሕዝብ ሁሉ--ምርጦችና ወርቆች የሚለውን አጓጉል ገለፃ አሽቀንጥሮ ጥሎ ማለት ነው--ያቀፈ ነው። ሀገር ሕዝብ ነው፣ እንዲሁ በደፈናው መሬት ወንዝ ተራራ ሸለቆ አይደለም። ስለዚህም ኢትዮጵያ ስንል የኢትዮጵያ ሕዝብን ያቀፈች ያካተተች፣ ለዚህም ቤት ሀገር የሆነች ምድርን ማለታችን ነው። ለዚህም ነው የጥቂቶች ኢትዮጵያ የብዙሃኑ አይደለችምና የሁላችንም መሆን አለባት ሲል ኢሕአፓ ሲታገል የባጀው። ዛሬም ቢሆን የወያኔና ዘራፊዎች ኢትዮጵያ የሕዝብ ኢትዮጵያ አይደለችም። ለነገሩ እነሱ ኢትዮጵያ ሲሉ በለበጣ ና ለማወናበድ እንጂ አደዬ አደዬ ከሚሉት ክልል የወጣ ስሜትም ፍቅርም የላቸውም። ወያኔ ሀገር ወዳድ ሳይሆን ክልሉን አፍቃሪ ጠባብ ብሄረተኛ ቡድን ነው። ዘረኛ ጎጠኛ ጠባብ ሁሉም መሰል ስያሜ ይገልጣ ቸዋል--ኢትዮጵያዊ ግን የሚለው ይጠናወታቸዋል። ሊለብሱት ሲሞክሩ ግንጥል ጌጥ ይሆንባቸ ዋል። ማ ቢወልድ ማን ይባልባቸዋል።

የኢሕአፓ አባላት ከሀገር በፊት ድርጅትን ያስቀድማሉ፣ ኢሕአፓ ኢትዮጵያዊነትን አላራመደም ብለው ሊከሱና ሊዋሹ የሚጥሩ ጥቂቶች አይደሉም። ይህ ግን አንድም ውሸት ሌላም የግንዛቤ ጉድለት ነው። የኢሕአፓ አባላት ድርጅታቸውን ማፍቀራቸው የሚጠበቅና መሆንም ያለበት

ነው:: ድርጅታቸውን የሚወዱትም ድርጀቱ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ጥቅም በመቆሙ ብቻ ነው:: መስመር ከለወጠና ለባዕድ ቅጥረኝነት ከጀመረው ወይም ለጥቅማ ጥቅም ሲል ለሀገር ጠላት ከተን በረከከ አባላት ድርጅቱን መውደድ ይቅርና ዞር ብለውም አያዩት:: ለዚህም ነው በየጊዜው ከውሰጥ የሚበቅሉ ሙጃዎችና አንጃዎችን መንቅለው የሚያወጧቸው:: ለኢሕአፓ ኢትዮጵያ ማለት በቅድሚያ ሕዝቧ ማለት ነው:: ሕዝብ ሲልም ጥቂቶች ምርጦችን፤ ከበርን ወይ ተማርን ባይ ዘብናኖችን ሳይሆን ሰፊውን ሰርቶ አደር ሕዝብ፤ አፈር ገፊውን ላቡን አፍሳሹን፤ ጥሮ ግሮ ኑሮን ሊገፋ የሚሞክረውን ማለት ነው:: ኢሕአፓ ሀገሬ የሚላት ለሁሉም ዜጎችዋ መመኪያና መጠሊያ፤ መኩሪያ የምትሆነውን ማለቱ ነው:: ትግል ሲጀምርም የሕዝብ እኩልነት ይከበር ያለው ሀገር ልትገነባ የምትችለው በዴሞክራሲና በዕኩልነት እንጂ በጭቆናና በትምክህት ወይም በጠባብ ከፋፋይ ብሄረተኛነት አይደለም ብሎ በማመኑ ነው:: ለዚህም ነው የሕዝብን መብትና እኩልነት የተፃረሩ ገዢዎች ሁሉ በመሰረቱ አሉትም አላሉትም ሀገርን የጎዱና እየጎዱም ያሉ ናቸው ብሎ በማመን አምርሮ የታገላቸውና እየታገለም ያለው:: አንዱን ዝቅተኛ ሌላውን ደግሞ ገዢ ብሎ በሕዝብ ደረጃ ልዩነትን ያሰፈነ አገዛዝ አንድነትን ሊያጠናክር ከቶም አይችልም-- የክፍፍልን መሰረተ ያኖራል እንጂ:: ለብሄረሰብ ቆመናል በሚልም የመብትን ፍትሐዊ ትግል ለክፍፈልና ግጭት፤ ለግንጠላና መለያየት የሚያውሉትንም ኢሕአፓ ሲታገላቸው ዓመታት አልፈዋል:: ኢሕአፓ ማንም ራሱን ነፃ አውጪ ብሎ የሰየመ ቡድን የዚያ ሕዝብ ብቸኛ ቀርቶ ህቀኛ ወኪልም ብሎ በደፈናው ተቀብሎ አያውቅም::

ዛሬ ከህቅ በተጣላ መንገድ ያን ሰው በላ አረመኔ መንግስቱ የተባለ ነፍሰ ገዳይና የወንጀል ጭፍሮ ቹን ሀገር ወዳድ ወይም ጀግና ብለው ሊያቀርቡ የተነሱትም ሁሉ የሀሰት ታሪክን እየፈተሉ ናቸ ው የምንለውም ለዚህ ነው:: መንግሥቱና ጭፍሮቹ ብዙ መቶሺ ዜጋን የጨፈጨፉ አውሬዎች ናቸው:: መንግስቱና ጭፍሮቹ ስንቱን ሀገር ወዳድ መኮንና ወታደር ያረዱ አረመኔዎች ናቸው:: መንግስቱና ጭፍሮቹ ባበለሹት ሁኔታ የተነሳ የሀገር አንድነት አፈር በልቷል:: መንግስቱና ጭፍ ሮቹ የቀይ ሽብር ሜአራማጆችና ስንቱን መቶ ሺ ወጣት የፈጁ ናቸው:: ታዲያ እንዴት በዚህ መንገድ ሀገርን ያደሙና የጎዱ ጉዶች ለሀገር አንድነት ቆሙ ተዋደቁ ይባላል? እንዴትስ ጀግና ሊባሉ ይሞከራል? የወያኔ መንጋስ ደግሞ በናቅፋ ተረግዞ በደደቢት መጨናገፍ ሲገባው ከተወለ ደ ጊዜ አንስቶ የኢትዮጵያን አንድነት ሲሰረስርና ሕዝብን በጅምላ ጠላት ብሎ ፈርጆ ስንቱን የትግራይ ወጣት በጥበትና በሕዝብ ጥላቻ ሲነዳና አልፎም ጭዳ ሲያደርግ ቆይቶ፤ በሀገር ግንጠላ ውም ገንጥሉልኝ ብሎ ባዕዳንን በመማፀን በታሪክ የመጀመሪያው አገዛዝ ሆኖ፤ ሀገርን በክልል ሸንሽኖና ሕዝብን በብሄረሰብ ከፋፍሎ እያለ አንዴትስ የኢትዮጵያ መንግሥት ነው ተብሎ በቁም ነገር ለአጋርነትና ለትብብር ይታጫል?

ኢሕአፓ ከተመሰረተ ጀምሮ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የገባውን ብሔራዊ ቃል ኪዳን ሳያፈርስ ታግሏል:: አንዳንዶች ከመጣው አገዛዝ ጋር ሲለጠፉና እስኪባረሩም ሕዝብን ሊበዘብዙ ሲጥሩ ኢሕአፓ በዚህ ቅሌታቸው አልገባም:: ምርጥነትን አቀንቅኖና ሕዝብንም ንቆና ክዶ ለሕዝብ

የማይበጁ እርምጃዎችን ሕዝባዊ ብሎ በማጭበርበር ከባለነፍጥ ጎን አልተኮለኮለም። ባዕዳን ሲያባ ብሉትም ካላችሁና ጥቅም ካገኙሁበት ብሎ ሀገርን የሚጎዳ ድርጊትን አልፈፀም፤ ለምሳሌ ቤተ እስራኤሎች ወደ እስራዔል ሊጓዙ ሲነሱ በነበረው ሀይልና በቁጥጥሩ ከነበሩ ቦታዎችም የተነሳ ሊያደናቅፍ ወይም እንደ ሌሎቹ ማለትም አንድ ደርግ፤ ወያኔና የኤርትራው ጀብሀ በሕዝብ ሽያጭ ሊሰማራ ሲችል በዚህ ቆሻሻ መንገድ ሲጓዝ አልተገኘም። እንደ ወያኔ የደቡብ ሱዳን ስደተኞችን ይዞ ለሱዳን እያሰረከበ በየመሸሩዕ ወይም እርሻ በግፍ አላስገደለም-- ስደተኞ ቹን በሰላም ወደ ጎንደር ሸኛቸው እንጂ። ቻይናም ከደርግ አብሩ ተባበሩ ስትል፤ ደቡብ የመንም ቢሮአችሁን እዘጋለሁ ከደርግ ካላበራችሁ ሲል ወግዱ አለ እንጂ ለጫናው አልተጎነበሰም። የነሄርማን ኮሽንንም ግፊት ተቀብሎ ለወያኔ እጁን አልሰጠም። እስቲ ሌሎች የኢትዮጵያን ጥቅም አስቀድመን የባዕዳንን ድለላ ሳንቀበል ቀርተን፤ ክብራችንን ጠብቀን ታገልን ይበሉ! በ1997 ምርጫ ወቅት እንኳን በአሜሪካና እንግሊዝ ግፊት የሕዝብን አድማ ያከሸፉት የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች ነን የሚሉት አልበሩም? ባለፈው ግንቦትስ የሕዝብ ክብር ተጠበቀ ወይስ ሕዝብ ለሐፍረት ተዳረገ ? ታሪክና ሀቅ የኢሕአፓን ፅኑ ኢትዮጵያዊነት ያረጋግጣሉ።ታሪክና ሀቅ የደርግን ሆነ የወያኔን በተጨባጭ ፀረ ኢትዮጵያነት ይመሰክራሉ። አንዱ አገዛዝ ኢትዮጵያ ወይ ሞት ቢልም ሞትን ለሕዝቧ በገፍ ሰጥቶ ሀገርን አሽመድዶ ለወያኔ አጋልጦ ፈራርሷል፡ መሪ ተብዬውም የአፄ ቴድሮስን መጨረሻ የራሱ ያደርጋል ብለው ፍፁም አማኝ ተከታዮቹ ሲጠብቁ ት ሸሽቶ ፈርጥጦ ዚምባብዌ ገብቷል፡ ይህ ታሪክ ብልሹ ደግሞ ቀና ታሪክያለው ይመስል ትዝታው እየተባለ መፅሀፍ ሲፃፍለትና ይህም ሲነበብለት እየታዘብን ነው። ሌላው ደግሞ ከተመ ሰረተ ጀምሮ የግንጠላን መፅሀፍ ሲደግም የቆየ ነውና በባዕዳን ድጋፍ ለስልጣን ሲበቃም ይህንኑ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ እነሆ እስከዛሬ በዘመቻ ላይ ነው።ወያኔ ስልጣን ሲይዝ ኢሕአፓ ለሹመት ሲሯሯጥና ጠባቦቹን ሲለማመን አልተገኘም። ዛሬ ተቃዋሚ ነን ከሚሉት ውስጥስ ስንቶ ቹ በወያኔ ያልቆሸሸ ታሪክ አለን ሊሉ ይችላሉ?

ኢሕአፓ ወደ ኋላ መለስ ብሎ ሀቅን ለማስፈር የተገደደው የውሸቱ ዘመቻና ጫጫታ በጣም ስለበ ዛና ዝምታም ውሸትን ሀቅ አድርጎ በመቀበል ደረጃ እንዳይወሰድ በሚል ነው። ኢሕአፓ በዋናው ጠላት በወያኔ ላይ በማተኮር ትግሉን አስተባብሮ ለማጠናከር ቢጥርም ቆሻሻ ታሪክ ያላቸው ይህ ቁሰላቸው ወይም ያፈሰሱት የንፁሀን ደም እያስጓራቸው ነጋ ጠባ በኢሕአፓ ላይ መዘመቱን ስለ መረጡ፤ወያኔም የሀሰት ጦረኞቹን በብዛት ቀጥሮ በኢሕአፓ ላይ ስላሰማራ ሀሰትን ሀሰት ውሸትን ውሸት ማለት የግድ ሆኖ ተገኝቷል፡ ወንጀለኞችም ከሕዝብ ጎራ ለመቀላቀል ከመሞከራቸው በፊት ንስሐ ይግቡ፤ ሕዝብን ይቅር በለን ይበሉ ማለቱም የግድ ሆኗል፡ ይባስ ብለው አንዳንዶቹ ኢሕአፓን ራሱን በሽብርና በሌላ ሌላም ሊከሱ መነሳታቸውን መታዘብ ችለናል፡ ከዋሹ አይቀር ይበላሹ ነው አንዳንዴ ። ኢሕአፓን በኢትዮጵያዊነት ስሜት ማነስ ሊከሱ የተነሱት ለሀገር ሲሉ ምን ትግል አካሂደዋል ብንል መልሱ አሳዛኝ ነው። ኢሕአፓ ከጠባቦቹ ጋር ሲፋለም ወይም በቦታው አልነበሩም ወይም ሕዝብን እየፈጀ ከነበረው ደርግ ጋር አብረው ሀገርን ሲጎዱ የነበሩ

ናቸው:: ወያኔም ለስልጣን ሲበቃ ከመ ቅፅበት የየብሄራቸውን ቡድን መስርተው አለና ለክፍፍል ብለው መሰለፋቸውን ታሪክ መዝግቧል:: በአዲስ አባባ በተደረገው የሽግግር ጉባዔ የነበረውን አሳፋሪ ትዕይንት ሕዝብ አይቷል፣ የወያኔ አጎብጓቢ ሆነው ሲጮኹ የነበሩትንም ታዝቧል::

ኢሕአፓ የሀገርን ጥቅም ማስቀደሙን  ከግንባር ምስረታ አንፃር የወሰዳቸው አቅዋሞች ምስክር ይሆኑለታል:: ከዚያም በፊት ደግሞ ሁሉን አቀፍ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይመስረት  ብሎ በመታገልና ለውሱን ድርጅታዊ ምቾትና ስልጣን ሲል ለአምባገነኖች ደጋፊ አለመሆኑ የሀገርና ሕዝብን ጥቅም ለማስቀደሙ በቂ ምስክር ነው:: ኢሕአፓ በቀይ ሽብርና ከዚያም በፊት ነፃ እርምጃ በተባለው ሲጨፈጨፍ የፍጅቱ ዋና አቀንቃኝ ከመሆን አልፈው በድርጊትም በየቀበ ሌው ስንቱን ከፈጁት መኢሶኖች ጋርም ቢሆን፣ በትግራይ መሬት በአሲምባ ከሻዕቢያ ጋር አብሮ ጦርነት በኢሕአሠ ላይ በመክፈት የመሪነት ሚና ከተጫወተው የቀድሞ ወያኔ መሪና አዲስ ቡድኑ ጋር፣ የደርግ አባል ከነበር ኮለኔል ጋር ወዘተ  ለሀገር ሲል በግንባር ተሳሰሮ ለመታገል ሞክሯል:: የግንባር ጥረቶችን ሁሉ ኢሕአፓ ረድቷል፣ተባብሯል:: አባላቱ ገንዘብም ጊዜም ሰጥተ ዋል:: ሀገራዊው ትግል የግድ ያለውን መቀበል ግድ ሆኖበት እንጂ፣ የሀገርን ጥቅም በማስቀደሙ እንጂ ኢሕአፓ ከነዚህ ዓይነቶቹ ጋር ና ጎን መሰለፍን የሚመርጥ አልነበረም:: ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ኢሕአፓ ህብረትን የማይፈልግ ወይም የሚመሰረትን ትስስር ካልወደደ የሚያፈርስ ነው ብለው የሚዋሹ አሉ:: በመጀመሪያ ደረጃ ኢሕአፓ ስለጠላውና ስለተቃወመው ብቻ የሚፈርስ ስብስብ ድሮውንም መሰረቱ የላላ ነበር ማለት ነው:: በሻዕቢያ አጋፋሪነትና በኦነግ የበላይነት አላዋቂ የውጭ ሀገር ያኔ ቅንጅት መሪዎችን በማደናገር በሆላንድ ተቋቀመ የተባለውን ትብብር ለነፃነት ና ለዴሞክራሲ የተባለ ስብስብን በወቅቱ ኢሕአፓ አባል ሆኖ የነበረበት ህብረት (ኢዴኃኅ) ተቃውሞት እንደነበር የሚታወቅ  ነው:: ትብብሩ ለኢትዮጵያ የማይበጅ ግን ለእንገንጠል ባዮች  የሚበጅ በመሆኑ ማለት ነው:: በስሙ ውስጥ እንኳን “ የኢትዮጵያ”  ማለትን መቀበል የተቃወ መ ስብስብ ነበርናም ከመወለዱ ተጨናግፏል:: ያዘነለትና ከል የለበሰለትም ብዙ ዜጋ አልነበረም: : ሀቁ ይህ እንጂ “ ምልዓተ ሕዝቡ አቅፎታል” ይባልለት የነበረውን ትብብር (ኤኤፍ ዲ) ኢሕአፓ ስለጠላው ብቻ አልፈረሰም:: ጠባቦች ገና ሲመሰረቱ ጀምሮ “ የሕዝባችን ብቸኛ ወኪል ና ተጠሪ ነን” ማለት ይወዳሉና በዚሁ ውሸታቸውና ቅዠታቸው ኢሕአፓ አጃቢያቸው መሆንን መርጦ አያውቅም:: ወያኔም ኢሕአሠ ከትግራይ ይውጣልኝ ሲልም ራሱን ብቸኛ የትግራይ ሕዝብ ተጠሪ ብሎ ሰይሞ ነው:: ዛሬ ኢሕአፓን በፀረ ትግሬነት ሊከሱ የተነሱትም የወያኔ ገደል ማሚቴዎች ሁሉ በመሰረቱወያኔን የታቃወመ ውይም የተቸ ሁሉ ትግሬን ሁሉ የጠላ ነው የሚለ ውን የሀሰት መልዕክት ለማስተላላፍ የሚለፉ ናቸው:: ኢሕአፓ ፀረ ትግሬ ለመሆን የሚችልበት ምንም ሁኔታ እንደሌለ ግን የትግራይ ሕዝብም በቅድሚያ ያውቃል:: ኢሕአፓ ኢትዮጵያዊ አይደለንም የሚል መርሀ ግብር ካላቸው ጋር ግንባር ብሎ ጊዜ ሊያጠፋም ሆነ ውዠንብር ሊፈጥ ር መቸም ፈልጎ አያውቅም:: ካለፈበት ተመክሮም በመነሳት ህብረት ህልውና ባላቸውና ካላቸው ድርጅቶች ጋር እንጂ ሶስት አራት አባሎች ካላቸው የይሰሙላ ቡድኖች ጋር ከሆነ ፋይዳ የለው

ም ሲልም አቅዋሙን ግልፅ አድርጓል። ይህን ማለቱ ህብረትን መቃወም ወይም መጥላት ሳይሆን ፍሬ ያለው ህብረትን መመስረት የሚቻለው ከዚህ በፊት ተሞክሮ ባልጠቀመ መንገድ ሳይሆን ከስህተትና ድክመት ተምሮ በአዲስና በተሻለ መንገድ ህብረትን ለመገንባት በመጣር ነው ብሎ ስለሚያምን ብቻ ነው።

ሀገሩን የሚያፈቅርና ሰብዕናውን የሚያከብር ሕዝብ ታሪኩን መንከባከብ አለበት። ሀገርን ካለፈው ትውልድ የተረከበው በተከፈለ ውድ መስዋዕትነት ነውናም ሀገሩን ማስከበርና መጠበቅ የተረካቢው ትውልድ ሀላፊነትና ግዴታ ይሆናል። ታሪክን መርሳት፤ አርበኞችንና ጀግኖችን ረስቶ ባንዳና ቡከኑን ጀግናና ነፃ አውጪ ብሎ ማቀፍ ሊደረግ ቀርቶ ሊያሰብም የሚገባው አይደለም። ኢሕአፓና ያ ትውልድ ታሪክ የጣለባቸውን ግዳጅ በድፍረት ተቀብለው ሊወጡ ሞክረዋል። ሙከራቸውም በነበረው ሁኔታና በነበራቸው ዕይታና እምነት መሰረት መሆኑም የሚጠበቅ መሆን ነበረበት። ሀገራቸው ኢትዮጵያ የምትበለፅግበትን መንገድ በመሻትና የጭቆና ስርዓትንም ለማስወገድ በመመኘት በተቃውሞ ጎዳና ሲጓዙ ይህ ውሳኔያቸው የሚያመጠባቸውን መከራና ስቃይ በተመለከተ ግንዛቤን ያጡ አልነበሩም። የትግሉ ነው ሕይወቴ በሚል መንፈስ ታገሉ እንጂ። ዛሬ እነዚህን ጅግኖች በማወደስና በመዘከር ፈንታ ከጭቆናና ጨቋኞች ጋር ሲተሻሹ የነበሩ ተመልሰው ሊከሱ ሊወነጅሏቸው ሲነሱ ማየቱና ማዳመጡ መቸም ህሊናን ይሰቀጥጣል። ሀገር ግዑዝ አይደለችም። ደጋግመን እንዳልነው ሀገር ማለት ሕዝብ ነው፤ ቅርስ ነው፤ ታሪክ ነው። ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለቡ ሀገሬ ኢትዮጵያ እያሉ መዝፈንና መጨፈር ሀገር መውደድን አይገልጥም። ሀገርን መውደድ ማለት ለሕዝብ ሲሉ መታገልን መሰዋትን ማስቀደም ማለት ነው፡ ኢሕአፓ በወቅቱ ኬለሎች የተለየው ለሀገሩ ሊሰዋ ዝግጁና ሞት አይፈሬ ሆኖ በትግሉ ሜዳም ደሙን ለሀገሩ በማፍሰሱ ነው። ታዲያ ማነው ዛሬ የኢሕአፓን ኢትዮጵያዊ ራዕይና ጀግንነት ሊፃረር የሞራል ብቃት ያለው? አፄ ኃይለሥላሴ ሀገር ጥለው ሲሸሹና አርበኞች የጣሊያንን ጦር በቆራጥነት ሲጋፈጡ ከትግሉ ሸሽተው የሄዱ ብዙዎቹ ከአፄውና ከእንግሊዝ ጦር ጋር ተመልሰው ለሰልጣን ሲበቁ የታገሉት እነ በላይ ዘለቀ ሲሰቀሉና ሌሎችም ሲገለሉ የተፃፈው ታሪክ አሳፋሪ ሆኖ ቀጥሏል። ባንዳ ሲሾም የታገለው ሲጠቃ ማየቱ በዝቶ ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላም ተብሏል። ይህ ምፀት ዛሬም ቀጥሎ የታገለውን ትውልድ እያወገዙና በኢሕአፓም ላይ ውሸትን እያሰራጩ የትላንት ነፍሰ ገዳዮችና ሀገርን ከቶም ያልጠቀሙ ጉዶች መድረኩን እያጨናነቁና ፤ ባንዳ ለባንዳም ጀግና እየተባባሉ ታሪክን ሊከልሱ ሲፍጭረጨሩ እያየን ነው። ውሸት እስከመቼ?

ኢትዮጵያ ዛሬ የምትፈልጋቸው ልጆች ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለቡ ሀገሬ ሀገሬ የሚሏትን ሳይሆን ሰንደቋን በልባቸው ተክለው ህይወታቸውን ሊለግሱላት የተነሱትን የሀቅ ታጋዮችና ጀግኖች ነው። ፍቅር ፍቅር ብለው ከጠላቷም ጋር ሳይቀር መተቃቀፍን የሚሰብኩትን ሳይሆን በጠላቷ ላይ መረራ ትግልን የሚያደራጁትንና የሚዋደቁላትን ነው። ዛሬ ኢትዮጵያ ህልውናዋ በከሀዲው የመለስ ዜናዊ ቡድን ለአደጋ ተጋልጦ ባለበት የትግልንና የመስዋዕትነትን ታሪክ መዘከርና

**ለአዲስ ትውልድ ማስጨበጥ እንጂ ለሀገር የሞቱትን በመቦጫጨቅና ገዳዮችና ለሀዲዎችን፤ ሽብርተኞችንና ፈርጣጮችን ለማሞገስ የተሰማሩትን ከቶም አትፈልጋቸውም፡፡ ሀገርን በማዋረድ ና በመጉዳትማ ወያኔ ራሱ ይበቃ አይደል!**

**ስለዚህም ውሸቱ ያብቃ! ሀገርን አሳልፎ ለከሀዲዎች መስጠቱ ያብቃ! መፍራት መራድ ያክትም! የጀግና አርበኞች ቆራጥነትን እንላበስ! የትግሉ ነው ሕይወቴን ጀግና ትውልድ ሰንደቅ እናውለ ብልብ! እውነቱ ተነግሮ ባለበቃበት ሀገር ለምንስ ይዋሻል? እስከመቼስ ይዋሻል?!**

**ይቀጥላል**